# የዕጽዋት አዳቃይ መብት መመሪያ ቁጥር 769/2013

መመሪያ ቁጥር 769/2013

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

በግብርና ሚኒስቴር የወጣ መመሪያ ቁጥር......

የግብርና ሚኒስቴር በዕፅዋት አዳቃይ መብት የወጣ አዋጅ ቁጥር 1068/2010 በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ የዕፅዋት አዳቃይ መብት መመሪያ ቁጥር 769/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **የዕጽዋት አዳቃይ መብት ተግባራዊ ስለሚሆንባቸው ሰብሎች ዝርዝር በተመለከተ**

ሚኒስቴሩ፤

1/ በአካባቢ፣በሰው፣በእንስሳት እና በዕጽዋት ብዝሃ ህይወት ጤንነትና ደህንነት አደጋ እንደሚያስከትሉ አግባብ ባለቸው ሌሎች ተቋማት በተደነገጉት የዕጽዋት ጀነራና ዓይነቴዎች ዝርዝር ተግባራዊ አያደርግም፣

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የዕጽዋት አዳቃይ መብት ተግባራዊ የሚደረግባቸው የዕጽዋት ጀነራና ዓይነቴዎችን ዝርዝር በተመለከተ የሚመለከታቸውን ተቋማት በተፈለገ ጊዜ ሁሉ ማጠየቅና ሚጋገጥ ይኖርበታል፡፡

3. **የዕጽዋት አዳቃይ መብት ማመልከቻ ስለሚቀርብበትና ስለሚመረመርበት ሁኔታ**

1/ ማንኛውም ሰው የዕጽዋት አዳቃይ መብት ለማግኘት በባለመብቱ ወይም በህጋዊ ወኪሉ የሚቀርበው ማመልከቻ የሚከተሉትን ማሟላት ይኖርበታል፤

ሀ/ የባለመብቱ ስምና አድራሻ፤

ለ/ ማመልከቻው በወኪል የሚቀርብ ከሆነ የወኪሉ ስምና አድራሻ፤

ሐ/ ዝርያው ቤተሰብ የሆነበት የሰብል ዓይነቴ እና የተለምዶ ስያሜ

መ/ እጩ የዝርያው ስያሜ

ሠ/ የአደቃዩ የዕጩ ዝርያው መለያ ኮድ፤

ረ/ ዕጩ ዝርያውን ያዳቀለው ወይም አግኝቶ ያበለጸገው አዳቃይ ስም፤

ሸ/ ዝርያው የተዳቀለበት ወይም የጎለበተበት ሁኔታ አጭር ማብራርያ፤

ቀ/ የአገር ወስጥ ብዝሃ ሕይወት በማጠቀም ለጎለበተ ዝርያ የአርክቦተ ፈቃድ፤

በ/ ዝርያው ከኢትዮጵያ ውጭ የመብት ጥበቃ ያገኘ ከሆነ ያገኘበትን አገር ስም፤

ተ/ አገሪቱ በተቀበለቻቸው እና አባል በሆነችባቸው ዓለም አቀፍ እና አህጉር አቀፍ ስምምነት መሰረት ለአመልካቹ ልዩ መብት የሚሰጥ ሚኛ ካለው ማክተት፤

ቸ/ ዝርያው በአገር ወስጥም ሆነ በውጭ አገር በገበያ የቆየበት ጊዜ፤

ነ/ የዝርያው ዘር ስለማጠበቁ ቅድሚያ ስምምነት፤

ወ/ ማመልከቻው በምርምር ተቋም ወይም በአርሶ/አርብቶ አደር ወይም በማህበረሰብ ወይም በወከላቸው አካል የቀረበ ከሆነ የባለቤትነት መብት እንዲሰጠው የጠየቀበት ደብዳቤ ከሚኒስቴሩ የማመልከቻ ቅጽ ጋር ተያይዞ መቅረብ ይኖርበታል፤

2/ የዕጽዋት አዳቃይ መብት ማመልከቻ ከተገቢ የማመልከቻ ክፍያ ሰነዶች ጋር ከሚከተሉት በአንዱ ለሚኒስቴሩ ሊቀርብ ይችላል፤

ሀ/ በፖስታ፤

ለ/ ሚኒስቴሩ ለዚህ ተግባር ባዘጋጀው ኤሌክትሮኒክ ማመልከቻ፤

ሐ/ በፋክስ፤

መ/ አካል፤

3/ ሚኒስቴሩ የቀረበወን የዕጽዋት አዳቃይ መብት ማመልከቻ በሚከተሉት መንገዶች ማለትም

ሀ/ የቀረበው ማመልከቻ በዚህ አንቀጽ ንዐስ አንቀጽ 1 ማሟላቱ መሆኑን፤

ለ/ ከማመልከቻው ጋር አባሪ ሆነው የቀረቡ ማስረጃዎችን ትክክለኛ መሆናቸውን፤

ሐ/ በማመልከቻው የተገለጸው የዝርያ ባህርይ ሚኒስቴሩ ለማመሳከሪያነት ካዘጋጀው የሌሎች የተጠበቁ ዝርያዎች የባህርይ መግለጫ ሰነድ ጋር በማመሳከር የተለየ ስለ መሆኑን፤

ይመረምራል፤

መ/ የቀረበው የባህርይ መግለጫ ሰነድ በሚኒስቴሩ ተቀባይነት ካገኘ የባህርይ ፍተሻ መካራ እንዲካሄድ ይወስናል፤

ሠ/ እንደ አስፈላጊነቱም መካራወን ሳይካሄድ በአመልካቹ የቀረበው የዝርያ የባህርይ መግለጫ ሪፖርት በሚኒስቴሩ እወቅና ባለው ተቋም የተሰራ ከሆነ በቀጥታ ሊቀበል ይችላል፤

**4. የዝርያ ባህርይ መለጫ ሰነድ እና አቀራረብ**

1/ የዝርያ ባህርይ መለጫ ሰነድ እንደ የሰብሎቹ ዓይነት ሚኒስቴር ማስርያ ቤቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ባገኘ አሰራር ባሟላ ሚልኩ እና የሚከተሉትን የተክል ክፍሎች በዓይነት /Type/ ለማየት የሚሞሉትን ባህርያት በተናጠል ወይም በጥቅል በማዝርዘር ያዘጋጃል፤

ሀ/ ቅጠል፤

ለ/ የተክሉ የሚራቢያ አካል፤

ሐ/ ግንዱ፤

መ/ ሥሩ፤

ሠ/ የአስተዳደግ ባሕርይው፤

ረ/ እንደ አስፈላጊነቱም ሌሎች ባህርያትን ማከተት ይቻላል፤

2/ የተክል ባህርያት መለጫ ሰነድ በዓይነት፣ በማጠን እና በዓይነት ማሰል ባህርያት ተዘርዝሮና ተዘጋጅቶ ለተገልጋዮች ተደራሽ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

**5. የአርሶ/አርብቶ አደር እና የማህበረሰብ ዝርያዎች የአዳቃይ መብት አሰጣጥ በሚከተለው ሚልኩ ተፋጻሚ ይሆናል፤**

1/ የአርሶ/አርብቶ አደር እና የማህበረሰብ ዝርያዎች የአዳቃይ መብት ጥበቃ ለማግኘት የሰብል ዓይነቴው በአገሪቱ የብዝሃ ሕይወት ተቋም

ሀ/ ማኛው ወይም ምንጩ /center of origin/ የኢትዮጵያ ስለሚሆኑ፤ ወይም

ለ/ በብዝሃ ሕይወት ተለያይነት /center of diversity/ ዝርዝር ወስጥ የተገለጸ ሲሆን ነው፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ሀ እና ለ ከተገለጹት ውጭ አርሶ/አርብቶ አደሮች በተናጠል ወይም በጋራ አንደ ማህበረሰብ የአዳቃይ መብት አንዲጠሰጣቸው ሲፈልጉ በአዋጁ አንቀጽ 4 ማሰረት መብታቸውን ከማጠቀም አይከለከሉም፡፡

**6. ማንኛውም አሚልካች እንደ አርሶ/አርብቶ አደር ወይም እንደ ማህበረሰብ የዝርያ የባለቤትነት መብት ለማግኘት የሚሚልከቻ አቀራረብና ዳሰሳ ጥናት ሂደት በሚከተለው ሚልኩ ተፈጻሚ ይሆናል፤**

1/ የመጀመሪያ ደረጃ ማሚልከቻውን ለቀበሌ የግብርና መዋቅር ያቀርባል፤

2/ ማሚልከቻውን ሲያቀርብ ዝርያው ከሌሎች ዝርያዎች የሚለይበትን ልዩ የባሕርይ መለጫ እና ሌሎች ተያያዥ ሚጃዎችን በዚህ መመሪያ በእዝል ተያይዞ በቀረበው ቅጽ ማሰረት ሞልቶ ያቀርባል፤

3/ የቀበሌ የግብርና መዋቅር የቀረበለትን ማሚልከቻ ማሰረት በማድረግ የባለቤትነት መብት ጥያቄ በቀረበበት ዕጩ የአካባቢ ዝርያ ላይ ቀበሌ አቀፍ ቅኝት በማካሄድ ተቃውሞ አለመኖሩን በሚያጋገጥ የድጋፍ ደብዳቤውን ይጽፍለታል፤

4/ በዚህ አንቀጽ ን/አንቀጽ 3 የወረዳ የግብርና መዋቅር የቀረበለትን የቀበሌ የድጋፍ ደብዳቤ መሰረት በመድረግ ወረዳ አቀፍ ቅኝት ያካሂዳል፤ ተቃውሞ አለመኖሩን በሚረጋገጥም የድጋፍ ደብዳቤውን ለዞን ወይም ለክልሉ የግብርና መዋቅር ይልካል፤

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 መሰረት የክልል ግብርና ቢሮ በስሩ የዘር ጥራት ተቆጣጣሪ መዋቅር ካለው በዚህ መዋቅር ከሌለው ግን የሰብል ልማትን በሚመለከተው ክፍል አማካይነት ዝርያው በሌሎች ዞኖች አለመኖሩን አጣርቶ ማስረጃዎችን ከማመልከቻው ጋር በማያያዝ ለግብርና ሚኒስቴር ይልካል፤

6/ የግብርና ሚኒስቴር በዚህ አንቀጽ ን/አንቀጽ 5 መሰረት የደረሰውን ማመልከቻና ሌሎች ተያያዥ ሚጃዎች መሰረት በመድረግ

ሀ/ የአገሪቱ የብዘሃ ሀይወት ተቋም ስለ ዕጩው የአካባቢ ዝርያ የይሁንታ አስተያየት እንዲሰጠው ይጠይቃል፤

ለ/ የአገሪቱ የብዘሃ ሕይወት ተቋም ሪፖርት ሲደርሰው ሚኒስቴሩ ስለቀረበው ዕጩ ዝርያ ተቃውሞ ስለአለመኖሩ ሰፊ ሽፋን ባለው ማናኛ ብዙሃን ጥሪ ያደርጋል፤ ማስታወቂያው የሚቆይበትን ጊዜ በማስታወቂያው ይገለጻል፤

ሐ/ በማስታወቂያው በተገለጸው የጊዜ ገደብ ወስጥ መቃወሚያ ካልቀረበ ሚኒሰቴሩ በቀረበው ዕጩ የአከባቢ ዝርያ ላይ የባሕርይ ፍተሻ ሙከራ እንዲካሄድ ያደርጋል፤

7/ ሚኒስቴሩ የአርሶ/አርብቶ አደር እና የማህበረሰብ ዝርያዎች የባሕርይ ፍተሻ ተግባርን

ሀ/ በራሱ የባሕርይ ፍተሻ ጣቢያ ላይ፤ ወይም

ለ/ ወክልና በሚሰጣቸው እና በየአካባቢው በሚገኙ የምርምር ማዕከላት ወይም ዩኒቨርስቲዎች ተፈጻሚ ሊያደርግ ይችላል፤

8/ የባህርይ ፍተሻ የሙከራ ማስ ዲዛይን እና የናሙና መጠን አወሳሰድ ሚኒስቴሩ ለየሰብሎቹ በሚያዘጋጀው የባህርይ ፍተሻ ፕሮቶኮል መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፤

9/ የአርሶ/አርብቶ/ማህበረስብ ዝርያ የውጥነት ደረጃ በኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ ለጥራቱ ለተገለጸ ዘር በወጣው የዝርያ ጥራት ለዝቅተኛው የዘር ደረጃ በተፈቀደው የአፍ ታይፕ መጠን መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፤

10/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 9 መሰረት ዝርያው ብቁ ሆኖ ከተገኘ እና ተቃዋሚ ካልቀረበ የአዳቃይ መብቱ ለአመልካቹ ይሰጠዋል፤

**7. ለመንግስት የምርምር ተቋም የዕጽዋት አዳቃይ መብት አሰጣጥ በሚከተለው ሜኩ ተፈጻሚ ይሆናል፤**

የባሕርይ ፍተሻ መስፈርቶችን አሟልቶ ለመብት ጥበቃ ዝግጁ የሆነን ዝርያ ለመንግሰት የምርምር ተቋም የባለቤትነት መብት ለመጠት መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች፤

1/ የዕጽዋት ዝርያ መብት እንዲሰጠው ሚኒስቴሩን በተቋሙ ስም የጠየቀበት ማመልከቻ፤

2/ ዝርያውን ያዳቀለው ወይም አግኝቶ ያበለጸገው የመንግስት የምርምር ማእከል ስም፤

3/ በምርምሩ ሂደት የተሳተፉ የመንግስት ተቋም አዳቃዮችና ሌሎች ባለሙያዎች ዝርዝርና በተቋሙ የተቀጠሩ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ፤

4/ ዝርያው በህዝብ ሃብት የፈለቀ ወይም የጎለበተ መሆኑን፤

5/ በዚህ አንቀጽ ን/አንቀጾች 1-4 የተዘረዘሩትን በሚጋገጥ ሚኒስቴሩ ዝርያው የህዝብ ሃብት መሆኑን ጠቅሶ የባለቤትነት መብት የምስክር ወረቀት ለተቋሙ ይሰጠዋል፡፡

**8. ሚኒስቴሩ ለህዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በሚከተሉት ሁኔታዎች በአዳቃይ መብት ላይ ገደብ ሊጥል ይችላል፤**

1/ አገር በቀል የዕጽዋት ብዝሃ ሕይወት ሃብት ክምችት ባለበት አካባበቢ እንዳይባዛ በማድረግ፤

2/ የተጠበቀ ዝርያ በሌሎች ዝርያዎች ላይ የሚያስከትለው አሉታዊ ተጽእኖ እስኪታወቅ ድረስ

ሀ/ በተወሰነ ስነምህዳር ወስጥ ብቻ እንዲባዛ በመፍቀድ፤

ለ/ ዝምድና ባላቸው የሰብል ቤተሰብ በሚሚቱበት አካባቢ እንዳይመረት በማድረግ፤

ሐ/ የግለላ ርቀትን ማስረት ያደረገ የአመራረት ሥርዓት እንዲከተል በማድረግ፤

መ/ መብቱ እንዲገደብ ያደረጉት ሁኔታዎች እስከነሳ ድረስ ፈጽሞ እንዳይመረት ወይም ተመርቶ ከተገኘም እንዳይሸጥ ወይም እንዳይሰራጭ በማድረግ

3/ ጥበቃ የተደረገለትን ዝርያ ዘር ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮለት የተጠቃሚውን ፍላጎት አባዝቶ ለማቅረብ ካልቻለ ወይም ለማቅረብ ፈቃደኛ ካልሆነ፤

**9. የግዴታ ፈቃድ ለሌላ ወገን ከማስጠቱ በፊት ማግስት ለህዝብ ጥቅም ሲባል የሚከተሉትን የድጋፍ አሚራጮች ለባለመብቱ ሊሰጥ ይችላል፤**

1/ የውጭ ምንዛሬ ግኝትና አጠቃቀምን አስመልክቶ ምቹ ሁኔታ በመፍጠር፤

2/ የማባዣ ማሳ ተደራሽነት በሚጋገጥ ወይም የኮንትራት ግብርና በአግባቡ በመተግበር፤

3/ ሌሎች አስፈላጊ ድጋፍ እና ግብዓቶች ተደራሽ የሚሆኑበትን ሁኔታ ማመቻቸትን ያጠቃልላል፡፡

**10. በአንቀጽ 8 መሰረት አስፈላጊው ድጋፍ አመቻችቶለት ሚኒስቴሩ መብቱ የተጠበቀ ዝርያ ባለቤት ላይ የግዴታ ፈቃድ ተግባራዊ እንዲሆን ከመወሰኑ በፊት፤**

1/ ለመብት ባለቤቱ ሃሳቡን እንዲገልጽ በጽሁፍ ያሳውቀዋል፤

2/ የዝርያው ባለቤት ከሚኒስቴሩ የተላከለትን የጽሁፍ ማስታወቂያ መሰረት በማድረግ በ15 የስራ ቀናት ወስጥ በጽሁፍ ምላሽ ማስጠት ይኖርበታል፤

3/ ሚኒስቴሩ ባለቤቱ ያቀረበወን ምላሽ መሰረት በማድረግ

ሀ/ የተጠቃሚውን ፍላጎት ለሟሟላት ፈቃደኛ ከሆነ የግዴታ ፈቃድን ተግባራዊ አያደርግም፤

ለ/ የተጠቃሚውን ፍላጎት ለሟሟት ፈቃደኛ ካልሆነ ግን የግዴታ ፈቃድን ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

**11. ሚኒስቴሩ የግዴታ ፍቃድ ለማስጠት የጠየቂዎችን አሚራረጥ በሚከተለው ማስፈርት መሰረት ተፈጻሚ ያደርጋል፤**

1/ ጠየቂው በዘር ማምረት የታደሰ የብቃት ሚጋገጫ የምስክር ወረቀት እና የንግድ ፈቃድ ያለው፤

2/ በአገሪቱ የዘር ገበያ ድርሻው ከሌሎች ሲነጻጸር የተሻለ ደረጃ ላይ የሚገኝ

3/ በብቃት ሚጋገጫ አሰጣጥና አስተዳደር መመሪያ መሰረት እና ከዚያም በላይ የሆነ የወስጥ የዘር ጥራት ቁጥጥር ስርዓት የዘረጋ፤

4/ በንጽጽር የተሻለ መጋዝን፣ሎጂስቲክስ /ትራንስፖርት/ እና የሰው ኃይል ያለው

5/ በተጠቃሚዎች እና በሌሎች ባለድርሻ አካላት በተሞላ የእርካታ ግብረ-መልስ ሪፖርት የተሻለ ወጤት ያስመዘገበ፤

6/ የግሉ ይዞታ ያለው ወይም በረጅም ጊዜ የተገባ የማሳ ኮንትራት ወል ያለው፤

7/ እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች ተጨማሪ ማስፈርቶች ማሟላት የሚችል፤

**12. ማንኛወም ሰው በአጁ አንቀጽ 17/2 መሰረት የዕጽዋት አዳቃይ መብት ለማገኘት በቀረበ ማመልከቻ ላይ ተቃወሞ በሚከተለው ሜለኩ ሊያቀርብ ይችላል፤**

1/ ተቃወሞ አቅራቢው ማመልከቻወን ሲያቀርብ በኤሌክትሮኒክስ፣ በአካል ወይም በፋክስ በማቅረብ ማመልከቻ ሊሆን ይችላል፤

2/ ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የደረሰወን ጥቆማ ማኘ በማድረግ በአምስት የስራ ቀናት ወስጥ ለባለመብቱ ያሳውቀዋል፤

3/ ባለመብቱ ከሚኒስቴሩ በደረሰው ጥቆማ መነሻ መሰረት በአስር የሥራ ቀናት ወስጥ ለሚኒስቴሩ ምላሽ ይሰጣል፤

4/ ሚኒስቴሩ የቀረበወን መቃወሚያ በህዝብ ጥቅም ላይ የሚያደርስወን ጉዳት

ሀ/ ከሰው፣ ከእንስሳት ወይም ከዕጽዋት ጤንነት፤

ለ/ ከምግብ እና ሥነ ምግብ ዋስትና፤

ሐ/ ከአካባቢ ደህንነት፤

መ/ ከሉዓላዊነት፤ ወይም

ሠ/ የብዝሃ ሕይወት ጥበቃና የአካባቢ ማህበረሰብ መብት፤

ረ/ ሌሎች ጉዳዮች ጋር የተያያዘ ስለመሆኑ መርምሮ ለማጣራት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብር ይሰራል፡፡

5/ ሚኒስቴሩ የቀረበው መቃወሚያ ዝርያወን በተመለከተ የዕጽዋት አዳቃይ መብት ለማስጠት የሚያስችሉ መስፈርቶችን አለማሟላቱ ጋር የተያያዘ ከሆነ፤

ሀ/ አዲስ መሆኑን ለሚረጋገጥ አዋጁ ከፈቀደው የጊዜ ገደብ በላይ ገበያ ላይ ያልዋለ መሆኑን ለማጣራት ልዩ ልዩ ጥናት/ምርመራ ያካሂዳል፤

ለ/ ጥበቃ እንዲደረግለት የቀረበው ዝርያ የተለየ መሆኑን ለሚረጋገጥ ተቃዋሚ አቅራቢው ካቀረበው ማመስከሪያ ጋር ያነጻጽራል፤

ሐ/ እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች ፍተሻዎችንም ተግባራዊ ሊያደርግ ይችላል፤

6/ የቀረበው መቃወሚያ ከባለቤትነት መብት የይገባኛል ጥያቄ ጋር የተያያዘ ከሆነ በተሻለ ባለመብት የሚያደርገወን ማስረጃዎችን ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

7/ ሚኒስቴሩ በቀረበው ተቃወሞ እና በባለብቱ ምላሽ መነሻነት ባደረገው ምርመራ መሰረት የሚከተሉትን ወሳኔዎች ሊሰጥ ይችላል፤

ሀ/ ተቃወሞወን ወድቅ ሊያደርገወና ማመልከቻወን በመቀበል ወደ ቀጣዩ የመብት አሰጣጥ ሂደት እንዲተላለፍ ያደርጋል፤ ወይም

ለ/ ተቃዎሞ ተቀባይነት የሚኖረው ከሆነ የቀረበወን የዕጽዋት አዳቃይ መብት ጥያቄ ወድቅ ሊያደርገው ይችላል፤

13. **የዕጽዋት አዳቃይ መብት ከተሰጠ በኋላ ለማስረዝ የቀረበን ማመልከቻ ለመመርመር እና ወሳኔ ለማስጠት ቀጥሎ በቀረበው ሂደት መሰረት ተግባራዊ ይሆናል፤**

1/ የቀረበው ማመልከቻ ከህዝብ ጥቅም ጉዳት ወይም መስፈርትን ካለሟሟላት ጋር የተያያዘ ከሆነ ማመልከቻወን ለመመርመር ሚኒሰቴሩ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 4 እና 5 የተጠቀሰው ሂደት ይከተላል፤

2/ ዝርያዎን ባለመዱስ ምክንያት የዕጽዋት አዳቃይ መብት ለማስረዝ የማቀርብ ማመልከቻን በሚከተለው መንገድ ይመረምራል፤

ሀ/ ሚኒስቴሩ የዝርያው ባለቤት ስለቀረረበት አቤቱታ በ15 ቀን በጽሁፍ ምላሽ እንዲሰጥ በማድረግ፤

ለ/ ሚኒስቴሩ ከዝርያው ባለቤት በቀረበለት ሪፖርት ማስረት የተጠበቀን ዝርያ ባህርያት ጠበቆ መቆየቱን በማስከ በማኘት በሚጋገጥ፤

ሐ/ በማስከ የተገኘወን ግብረ ሜለስ ማስረት በማድረግ ከዝርያው ናሙና ወስዶ በማስከ ወይም በቤተሞከራ ድጋሚ ፍተሻ በማድረግ፤

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ማስረት ተገቢው ምርመራ ከተከናወነ በኋላ ሚኒስቴሩ የሚሰጠው ወሳኔ ከሚከተሉት አንዱ ሊሆን ይችላል፤

ሀ/ ማመልከቻውን ወድቅ ማድረግና መጀመሪያ የተሰጠውን መብት ማጽናት፤ ወይም

ለ/ በማመልከቻው ማስረት ቀደሞ የተሰጠውን መብት ማስረዝ ብቻ፤ ወይም

ሐ/ በማመልከቻው ማስረት ቀደሞ የተሰጠውን መብት ማስረዝ እና አግባብ ለሆነው አካል ማስተላለፍ፤

**14. የእጽዋት አዳቃይ መብት ለማግኘት ለባህርይ ፍተሻ ተግባር የሚውል ናሙና ማጠን ሚኒስቴሩ ለየሰብሉ ዓይነቴው በሚዘጋጀው የአሰራር ድንብ ማስረት ተፈጻሚ ይሆናል፤**

15. ጥበቃ የተደረገለትን ዝርያ ዘር ናሙና ማጠን፣የቆይታ ጊዜ እና የሚከማቹ ዓይነት እና አቀማመጥ በተመለከተ እንደየ ዕጽዋት ዝርያ ዓይነቱ በሚኒስቴሩ የአሰራራ ደንብ /by-law/ ላይ የሚወሰን ይሆናል፡፡

16. ይህ መመሪያ ከየካቲት 19 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

ዑመር ሁሴን

ግብርና ሚኒስትር